# የሰለቸነው ፖለቲካ

በአሜሪካ ድምጽ ራዲዮ ሔኖክ ሰማእግዜር ሰኞ መስከረም ፳፫ ቀን ፳፻፫ ዓ. ም. የመድረክ አመራር አባላት ከአንድ ቀን በፊት በዋሽንግተን ዲሲ ስላደረጉት ሕዝባዊ ስብሰባ ሲዘግብ የሚከተሉት ሐረጋትና ዐረፍተ ነገሮች ሰላም ነሱኝ።

፩ኛ/ መድረኩን ይመሩት የነበሩት ሰው፤ የኢሕአፓ ወጣት ክንፍ አባላት ከፍ ያለ ድምጽ ሲያሰሙ፦ ሴኩሪቲ [ጥበቃ] ጥራ ካሉ በኋላ **የሰለቸነው ፖለቲካ** ብለው ተናገሩ። እኚህ ሰው ለምን እንዲህ ተናገሩ? ለሚለው የጎሊናዬ ጥያቄ መልስ ለማግኘት ብዙ ጣርኩ ግን አላውቃቸውምና መልስ አላገኘሁም። የምታውቋቸው ካላችሁ ገላግሉኝ። እኔ ግን በነዚህ ግምቶች ራሴን ለጊዜው እረፍ ብዬዋለሁ። የመጀመሪያው ግምቴ እኚህ ሰው የኢሕአፓን አባላት ገዳይ አሊያም አስገዳይ ነበሩ የሚል ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ በዚያ ዘመን በሕይወት ያልኖሩ ሰው ናቸው የሚል ነው። ምክንያቱም የዛሬ ፳ ዓመት በአደባባይ ለተፈጸመው ግድያ የመታሰቢያ ፕሮግራሞችና ተቃውሞዎች ካደረጉ፤ ከዛሬ ፴ እስከ ፴፭ ዓመት በፊት በአደባባይ ለተፈጸሙ ግድያዎች ተቃውሞ ማቅረብን የሰለቸነው ፖለቲካ የሚያሰኝበት ምክንያቱ በፍጹም ሊገባኝ አልቻለም።

፪ኛ/ በዚህ ስብሰባ ላይ አቶ ሰዬ አብርሃ በኢሕአዴግ አስተዳደር ወቅት በኃላፊነት ሲሠሩ ለተፈጸመው የሙብት ጥሠቶችና አግባብነት ለሌላቸው የሕዝብን ጥቅም ያላስጠበቁ ውሳኔዎች ኃላፊነት እወስዳለሁ ብለዋል። ይኸንን ዐረፍተ ነገር ለሦስትና ዐራት መቶ ታዳሚዎች ሳይሆን ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲደግሙት የጎሊና ግዴታ አለብዎት እላቸዋለሁ።

ከኢሕአፓ ጋር ተጋድለናል፣ ተዋግተናል፣ ሕይወት ጠፍቷል አዝናለሁ፤ ግን ከሁሉም ወገን ነው የጠፋው። አንድ ወገን ጠያቂ አንድ ወገን ተጠያቂ የሚሆንበት ምክንያት የለም ብለዋል። ግሩም ነው። ኢሕአዴግ ደርግን ከሥልጣን ሲያስወግድ እየሞተ ብቻ ነበር የታገለው? ከሁለቱም ወገን ሕይወት ጠፍቷል፤ ነገር ግን ከደርግ ወገኖች ሕይወት ማለፉ፣ ደርግን ከወንጀለኛነት ነጻ አላደረገውም። ዋናው ጉዳይ ሕይወት እንዲጠፋ ምክንያት የሆነው መነሻ አይደለምን? እናም ምነው ከኢሕአፓ ጋር ለመጋደላቸው መነሻውን ለማብራራት አልደፍር አሉ?

የሞቱትስ እሺ ይረሱ፤ ስለ ተጋዙትስ የሚሉን የለዎትም?

፫ኛ/ አቶ መረራ ጉዲና ደግሞ፤ ሒሳብ የማወራረድ ፖለቲካ ማብቃት አለበት ብለው አበክረው ተከራክረዋል። እርግጥ ነው የፖለቲካ ሒሳብ እንደ ዖሪት ሕግ ዐይን ያጠፋ ዐይኑ ይጥፋ ተብሎ የሚወራረድ እንዳልሆነ ይታወቃል። ነገር ግን ዐይን ያጠፋ፤ ዐይን ማጥፋቱ ተረጋግጦ፤ አጥፍቻለሁና ለዚያም ተገቢውን ፍርድ ከሕዝብ ለመቀበል ዝግጁ ነኝ ብሎ የማወራረድ ግዴታ አለበት። እርስዎም ቢሆኑ ከአምቦና አካባቢው ሕዝብ ማወራረድ የሚገባዎት ብዙ ሒሳብ አለና ዝግጁ ሊሆኑ ይገባል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ዝም ማለት አላዋቂነት መስሏችሁ ከሆነ በጣም ተሳስታችኋል። የማያውቀው ጉዳይ የለም፤ ለዕለታዊ የፖለቲካ ፍጆታ ተጠቃሚዎች እንዳይውል በማሰብ እንጂ።

እናም የዛሬ ፴፭ ዓመት ስለተገደለብኝ አባቴ ዛሬ ብጮህ፤ ያለ አባት ማደግን የማያውቅ ብቻ ነው ወጊድልኝ የሚለኝ። ከቤት እመቤትነት ወደ ሴተኛ አዳሪነት ልጆች ለማሳደግ አእምሮን አሳምኖ መኖር ምን ያህል አለት እንደሆነ የሚያውቀው የሞከረው ብቻ ነው። ጠላ ሸጣ አሳድጋ፤ ውለታዋን ለመመለስ የተዘጋጁ ታማኝ ልጆቿ ከበሯ ላይ ጨንቅላታቸው በጥይት ተነድሎ ያየችን እናት፤ ስለ ልጆችሽ አታንሺ የሚላት ካለ ከገዳዩ የባሰ አረመኔ ነው።